# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

የዓቢይ ጾም ሁለተኛው ሰንበት «ቅድስት» ይባላል።

የዓቢይ ጾም ሁለተኛው ሰንበት «ቅድስት» ይባላል። ስያሜው የቅዱስ ያሬድ ሲሆን የመዝሙሩ ርዕስ የጾመ ድጓው መክፈያ ሆኖ የሚጠራበት ስም ነው። ከቅድስት ሰኞ ጀምሮ እስከ ጾመ ዐርብዕ ያለው ጾመ ኢየሱስ ይባላል። ከዚህ ሰኞ ጀምሮ ለእግዚአብሔር መገዛት፤ መስገድ እንድንችል ለእግዚአብሔር መቀደስ ስለሚገባን ቅድስናን ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች። ለዚህም በመዝሙሯ በቅዳሴዋ ሁሉ ቅድስናን የሚያንጸባርቁ ቃላት ሞልተዋል። በዚህ ቀን ስለ ክብረ ሰንበት፣ ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ይዘመራል። በቅዳሴ ጊዜም የሚነበቡት ቅዱሳት መጻሕፍትም ስለ ቅድስና የሚያስተምሩ ናቸው።

## የዕለቱ ምስባክ

እግዚአብሔርሰ ሰማያተ ገብረ
አሚን ወሰናይት ቅድሜሁ
ቅድሳት ወዕበየ ስብሐት ውስተ መቅደሱ

እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሰራ
ምስጋና ውበት በፊቱ ነው
ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው።

መዝ ፺፭ (፺፮)፥፭

ወንጌል፥ ማቴ ፳፫፥፲፫-፳፭
ቅዳሴ፥ የኤጲፋንዮስ ቅዳሴ (ዐቢይ)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ግነዩ ለእግዚአብሔር ወጸውኡ ስሙ
(እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ)

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ተሰሎ ፬፥፩-፲፫ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፫ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፥፲፯-፴ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

# ቅድስና

ቅዱስ ተብሎ የሚመሰገን፣ የቅድስና ምንጭ፣ በቅድስናው የተቀደሰ፣ ፍጥረት የለገሰችው ቅድስና ከፍጥረት የተሰጠ ቅድስና የሌለው፣ በቅድስና የሚኖር፣ ቅድስና የባሕሪዩ የሆነ፣ ቅዱሳንን የሚቀድስ፣ ቅዱሰ ቅዱሳን እግዚአብሔር ነው። በእስራኤል የመዝሙር መጽሐፍ «አቤቱ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው?» ተብሎ እንደተጻፈ አምላከ አማልክት እግዚአ አጋዕዝት ጌታ በቅድስናው የከበረ ነው። ምስጋናውም ቅዱስ እንደሆነ ያየውና የሰማው ኢሳይያስ ስሙን ቅዱስ ብሎ ጠርቶታል (ኢሳ ፮፥፩-፲ ። ኢሳ ፵፥፳፭)። ቅዱስ ዮሐንስም «አንተ ብቻ ቅዱስ ነህ» ብለው መላእክት በሰማይ በባሪያው በሙሴ መዝሙር እንደሚያመሰግኑት ጽፎልናል (ራዕ ፲፭፥፬)። እግዚአብሔር የሰማት ሐናም «እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና ... ከአንተም በቀር ቅዱስ የለም» ብላ ዘምራለች (፩ኛ ሳሙ ፪፥፪-፫)። ፈጣሪ ራሱ ራሱን እንዲህ ሲል ገለጠው «እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» (ዘሌ ፲፱፥፪ ። ፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፮)።

በአፈ መላእክት የሚጠራውና የሚቀደሰው በልሳነ ሰብእም (በሰዎች አንደበት) «ይትቀደስ ስምከ - ስምህ ይቀደስ» እየተባለ የሚጠራው ስሙ ቅዱስ ነው። ስሙም ከስሞች ሁሉ በላይ ስለሆነ ጌታችንም እራሱን ሲገልጥ «እኔ ቅዱስ ነኝ» ብሎ ቅዱስ መሆኑን ተናገረ። ነብዩም «ስሙ ቅዱስ የሆነ ከፍ ያለው ልዑል» ብሎ ይጠራዋል (ኢሳ ፶፯፥፲፭)። ባለቤቱም «ቅዱስ ስሜን አረከሱ ... እኔም ስለ ቅዱስ ስሜ ስል እራራለሁ» አለ (ሕዝ ፴፮፥፳-፳፩)። ቅዱሱን የጸነሰችው የቅዱሱ እናትም «ወቅዱስ ስሙ - ስሙ ቅዱስ ነው» አለች (ሉቃ ፩፥፵፱)። ቅዱሱም ለዘለዓለም በስሙ ቅዱስ ቅዱስ እየተባለ ይመሰገናል (ኢሳ ፮፥፫ ። ራዕ ፬፥፰)።

ስሙ ቅዱስ የሆነ ፈጣሪም በቅድስናው የእርሱ የሆኑትን ይቀድሳል (ዘጸ ፳፰፥፵፩)። ስሙ የሚጠራበትን በጐ የሚነገርበትን ሥጋው ወደሙ የሚፈተትበትን ይቀድሳል (ዘጸ ፫፥፭)። የመለኮታዊ ሥራው ፍጹምነት ምልክት የሆነችውን ዕለተ እረፍት እለተ አምልኮ ሰንበትንም የቀደሰ እርሱ ነው (ዘፍ ፪፥፫)። የምንሰጠውን መባ የሚቀድስ፣ ንዋየ ቅድሳትን የሚቀድስ ሁሉን የሚቀድስ እርሱ ነው (ኢያሱ ፮፥፲፱)።

እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ የእግዚአብሔር የሆኑ ምእመናንም ቅዱሳን ናቸው። ጌታችን «በእውነት ቀድሳቸው» እንዳለ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን በፈጣሪዋ እውነት በመሲሁ ደም ከኃጢአትዋ ተቀድሳ «ቅዱሳን ሁኑ» ያለው ንጉሥ ተከታይ ሆናለች።

አንባቢ ሆይ፥
በክርስቶስ ብትኖር ቅዱስ ልትሆን እንደምትችል ታውቃለህን (፩ኛ ቆሮ ፩፥፪)? እንዲሁም ቁጥር ፴። በፈጣሪህ ጽድቅ በኑሮህ ልትቀደስ እንደምትችል (ዮሐ ፲፯፥፲፯-፲፱)። ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ተወልደህ የቀዳማዊ አዳምን መርገም ፈጣሪህ ጥሎልህ ቅዱሳንን በቀደሰው ተቀድሰህ ለመኖር ሁለተኛ በሐዲስ ተፈጥሮ በክርስቶስ መፈጠርን ታውቃለህ። በቅዳሴ ጊዜ አንደኛው ዲያቆን ያነበበው መልእክት «የእግዚአብሔር ፈቃድ መቀደሳችሁ ነውና ከዝሙት እንድትርቁ ... እናንተ እያንዳንዱ የራሱን እቃ (አካል) በቅድስና በክብር ያገኝ ዘንድ እንዲያውቅ ... ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር ለቅድስናው ጠርቶታል» ይላል (፩ኛ ተሰሎ ፬፥፫-፰)።

በረዳቱ ዲያቆን የተነበበው መልእክትም «እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ ሁኑ» ይላል። በረዳቱ ቄስ የተነበበውም «የተቀደሰውን አታርክሱ» ይላል (፩ኛ ጴጥ ፩፥፲፫-፲፯ ። የሐዋ ፲፥፲፪-፴)። ቅዱስ ያሬድም ስለ ቅድስና ዘምሯል። አንተስ በጥምቀት የእግዚአብሔር ማደሪያ (ቤተ መቅደስ) የሆነ አካልህን ታረክሳለህን ወይንስ ተቀድሰሃል? በል ተቀደስ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።